# «ሃገርን ለበታትን የሚችለው የነበሩ ቀስሎችን የሚብሱበት ሁኔታ ሲፈጠር ነው»

የቀድሞ የአፌድሪ ፕረዝደንት ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ በተለያዩ ሃገራዊ ገዳዮች ዙርያ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ያደረገትን ቀለምልልስ ባለፈው እትም ማቅረባችን ይታወሳል:: ቀጣዩን ክፍል እንደሚከተለው ቀርበዋል::

***ህዝባዊ:*** *በሽግግሩ ወቅት ኦነግ ፈፅሞታል የሚባል ጥፋት ነበር:: ይኸውም በወተር፣ በበደኖና ሌሎች በምስራቅ ሃረርጌ የተፈፀሙ እልቂቶች ናቸው:: እነዚህ እልቂቶች አሁን አሁን በኢህአዴግ የተቀናበሩ እንጂ በትክክል በኦነግ የተፈፀሙ አልነበሩም የሚል ወሬ ይሰማል:: ስለዚህ እርስዎ የሚሉት ነገር ይኖር ይሆን?*

**ዶ/ር ነጋሶ:** በሽግግር ወቅት የኦነግ ካድሬዎችና ሰራዊት አባላት በተለያዩ ቦታዎች ወንጀል ፈጽመዋል:: ከዚህ በላይ እንደጠቀስኩት በዘመዶቼም ላይ ወንጀል ፈጽመዋል:: እነዚህ ወንጀሎች የተፈፀሙት:: የአንድን ወይም የሁለትን ብሔረሰቦች ተወላጆችን ማዕከል በማድረግ አልነበረም:: ኦሮሞዎችን ጨምሮ እሱን በማይደግፉና የኦህዴድ/ኢህአዴግ ደጋፊዎች በሆኑት ላይ ወንጀሎች ተፈጽመዋል:: የኦነግ ድክመት የነበረው እንደሚመስለኝ የህዝባዊ ትግል ምን እንደሆነ የማያውቁትንና የህዝባዊ ትግል ስነ ምግባር የሌላቸውን ሰዎች ማግበስበሰ ነው:: የላይኛው አመራር በታችኛው ካድሬዎቹ፣ አባላቱና ደጋፊዎቹ ላይ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር የነበረው አልመሰለኝም:: በጥፋተኞች ላይ የማስተካከያ እርምጃዎችን ሲወሰድ የነበረ አይመሰለኝም:: በመሆኑም ብዙ ጥፋቶች ተከስተዋል:: ከነዚህ ውስጥ ትልቁ ወንጀል የበደኖው እልቂት ነው:: ይህን በተመለከተ የሽግግሩ ም/ቤት የማጣራት እንቅስቃሴ አድርጐ ሪፓርቱ ቀርቦ በተወያየንበት ጊዜ በፓርላማው የነበሩ የኦነግ አመራር አባላት ወንጀሉ በኦነግ ሰዎች መፈፀሙን አምነዋል:: በወተር የተፈፀመው ወንጀል በኦህዴድ ሰራዊት አባላት ነበር:: በዚያን ጊዜም ሆነ ከዚያ በኋላ የኦነግም ሆነ የኦህዴድ የታችኛው መዋቅር አባላት የተለያዩ ወንጀሎችን ፈጽመዋል:: ኦህዴድን በተመለከተ ምን ዓይነት ወንጀሎች ሲፈፀሙ እንደነበር በ1989 ዓ.ም ግምገማችን አይተናል:: የኦነግም ሆነ እኛም የኢህአዴግ/ኦህዴድ አመራር አባላት የኛ አባላት ወንጀሎች መፈፀማቸውን በይፋ አምነን በይፋ ህዝቡን ይቅርታ አልጠየቅንም:: የተለያዩ ወንጀሎች በኢህአዴግ ተቀነባብረው በኦነግ ላይ ተላከኩ የሚለውን ውንጀላ መቀበል አሁን ያዳግተኛል:: እንደ እውነቱ ከሆነ በፀጥታና የመከላከያ መዋቅሮቻችንን ስራን በቅርብ ለመከታተል ዕድል ስላልነበረኝ ሲደረጉ የነበሩትን ነገሮች አላውቅም ቢሆንም በፖለቲካ ትግል ውስጥ መወነጃጀል የተለመደ መጥፎ ባህል አለ:: እውነታው ግን ይፋ የሚሆነው እውነተኛ የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ሲመሰረትና ህዝቡ የሚያውቀውን ሁሉ ለመተንፈስ ሁኔታው ሲመቻችለት ነው:: እስከዚያ ግን ገለልተኛ የሆነ አካል ተቋቁሞ ጥናት ቢያካሂድና የጥናቱን ውጤት ይፋ ቢያደርግ ይረዳል:: በተጨማሪም የሽብርተኝነት ወንጀል በመፈፀም በየጊዜው የሚታሰሩ ግለሰቦች ጉዳይ በፍ/ቤት ሲታይ ውጤቱ ለህዝብ ይፋ መሆን አለበት:: ይህ ወንጀል ተፈፀመ፣ ወንጀሉን የፈፀሙት ግለሰቦች እነዚህ ናቸው ብሎ በቴሌቪዥን የፕሮፖጋንዳ ዝግጅት ማቅረብ ብቻ አይበቃም:: እነዚ ሰዎች ባፋጣኝ ወደ ፍ/ቤት ቀርበው ጥፋተኝነታቸው ከታወቀ ተገቢውን ቅጣት ማግኘት አለባቸው በስህተት ተወንጅለው ከሆነም ነፃ መውጣት ብቻ ሳይሆን ካሳም የሚጠይቁበት ሁኔታ መፈጠር አለበት:: ሰዎችን ያለበቂ መረጃ መወንጀልና ማሰር፣ ከዚያም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ጉዳዩ በይፋ ሳይነገር በድብቅ መልቀቅ ስህተት ነው:: የዚህ ዓይነት ስህተት ወይ የችሎታ ማነስን ወይም ደግሞ መንግስት ራሱ ወንጀል ፈጽሞ በውሸት በሌሎች ላይ አላክኮ የፖለቲካ ጠቀሚታ ለማግኘት የተጠቀመበት ነው የሚለውን ክስ ያጠናክራል:: ከዚህ በላይ እንዳልኩኝ ለስልጣን በሚደረገው የፖለቲካ ፉክክር ውስጥ መጥፎ የመወነጃጀል ባህሎች ታይተዋል:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ የኦነግና የኢህአዴግን መወነጃጀል ብቻ ማየት የለብንም:: በኦሮሚያ ብዙ የተለያዩ የኦሮሞም ሆነ የኦሮሞ ያልሆኑ ኃይሎች ወይም ድርጅቶች እንደሚንቀሳቀሱ ማስታወስ ያስፈልጋል:: የኦነግ ተቀናቃኞች የሆኑ የኦሮሞ ድርጅቶች አሉ:: የኦሮሞን ህዝብ ትግል ለማጉደፍ የሚጥሩ ኃይሎችም አሉ::

***ህዝባዊ:*** *በዛን ወቅት ኦነግና ሌሎች የሽግግሩ አባል ድርጅቶች ሽግግሩን ለቀዋል:: እነዚህ ድርጅቶች የኢህአዴግን አጠቃላይ ዲሞክራሲያዊ አያያዝ ይነቅፉ ነበር:: እርስዎ አሁን ተመልሰው ሲያዩት ጉድለት የሚሉት አያያዝ ይኖር ይሆን?*

**ዶ/ር ነጋሶ:** አዎን የሽግግር መንግስትን ከመሰረቱት ድርጅቶች ኦነግን ጨምሮ ሽግግሩን ለቀዋል:: አንዳንዶቹ ለምሳሌ ኦነግ የኢህአዴግ አያያዝ ዴሞክራሲያዊ አልነበረም የሚል ነቀፌታ ያቀርባሉ:: አንዳንዶቹ ደግሞ በፓሪሱ ስብሰባ ላይ ለምን ተሳተፋችሁ ተብለው ከሽግግር መንግስቱ እንዲገለሉ የተደረጉት:: በኔ እምነት አንዳንድ የችግር መንስኤ የሆኑ ሁኔታዎች ነበሩ:: ለምሳሌ ኦነግ በዚያን ጊዜ ተግባራዊ አደርጋለሁ ብሎ የያዘው ፕሮግራም ኦሮሚያን ነፃ በማውጣት ነፃ የኦሮሚያን ሪፐብሊክ እመሰርታለሁ የሚል ነበር:: በዚያን ጊዜ የነበረው የኦነግ አመራር ይህን ፕሮግራም ዓላማ ሳይቀይር ነው የሽግግሩን ቻርተር ያፀደቀውና የፈረመው:: ቻርተሩ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ የሆነች ኢትዮጵያን በጋራ እንገነባለን ይላል:: መሆን የነበረበት ወይ ፕሮግራሙን ከቻርተሩ ጋር በሚጣጣም መልኩ ማስተካከል ወይም ደግሞ ፕሮግራሙን ይዞ በተቃዋሚነት መቀጠል ነው:: ይህ በኦነግ በኩል ባለመደረጉ ችግሮች

ተፈጥረዋል፡፡ በኢህአዴግም በኩል ላይ የዘረዘርኩአቸው ስህተቶች ነበሩ፡፡ ማለትም ኢህአዴግ በራሱ ፕሮግራም ውስጥ ያስቀመጣቸውን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ቅድመ ሁኔታዎችንና መስፈርቶችን በማስቀመጥ ድርጅቶች እንዲገለሉ አድርጐአል፡፡ ኢህአዴግ ሲንቀሳቀስ የነበረው የመንግስት ስልጣንን ብቻውን አጠቃሎ መያዝ ነበር፡፡ ስልጣንን ከሌሎች ጋር ለመጋራት ፍላጐት ከነበረውም እሱን ቻሌንጅ ሊያደርጉ ከሚችሉት ወይም ተቀናቃኙ ከሆኑት ጋር አልነበረም፡፡ ስለሆነም ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ኢ ዲሞክራሲያዊ መሆኑ አልቀረም፡፡ ይህ እኔም የተጋራሁት ጥፋት ነው፡፡ ዲሞክራሲያዊ አልነበርንም ቶሎራንት አልነበርንም በተለይ ኦነግን እንጠላው ነበር፡፡ በኦሮሚያ ኦነግ ከፍተኛ ተሰሚነትን ተቀባይነት ነበረው፡፡ ቻሌንጅ ልናደርገው ስላልቻልን በኢ ዲሞክራሲያዊ አሰራር ከሽግግሩ እንዲገለል አድርገናል፡፡

***ህዝባዊ:*** *ዶክተር ነጋሶ በሽግግሩ ወቅት የማስታወቅያ ሚኒስቴር ሆነው ሰርተዋል፡፡ ማስታወቅያ ሚኒስቴርን በሚመሩበት ጊዜ እርስዎ የፈፀሙት መልካም ነው ብለው የሚያስቡት ነገር ምንድን ነው? አሁን ተመልሰው ሲያዩት ይህን ባደርግ መልካም ነበር የሚሉትስ ይኖራልን?*

**ዶ/ር ነጋሶ:** ማስታወቂያ ሚኒስቴር በነበርኩ ጊዜ በፕሬስ ቅድመ ምርመራ (Censorship) እንዲቀርና አሁን እየተሰራበት ያለው የፕሬስ ህግ እንዲረቀቅና እንዲፀድቅ ለማድረግ ሲካሄድ በነበረው እንቅስቃሴ ንቁ ተሳትፎ አድርጌአለሁ፡፡ ገና አሁን ከብዙ ዓመታት በኋላ ተግባራዊ ሊሆን የታሰበው የብሮድካስት ሕግም የወጣው እኔ ማስታወቂያ ሚኒስቴር በነበርኩ ጊዜ ነው፡፡ የፕሬስ ህጉ ተግባራዊ ቢሆንም ብሮድካስት ሕጉ ቶሎ ተግባራዊ እንዲሆን በቂ ግፊት አላደረግሁም ይህ ያሳዝነኛል፡፡ በዚያን ጊዜ ከፍተኛ ትኩረት የሰጠሁት ለአቅም ግንባታ ስራ ነበር፡፡ ኢዜአን ዘመናዊና በኮምፒውተር የታገዘ ድርጅት እንዲሆን፣ ኢዚአና የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አሁን ያሉበን ህንፃዎች እንዲያገኙ፣ የኢትዮጵያ ራድዮ ወደ አየር ጤና እንዲዛወር፣ የሚድያ ማሰልጠኛ ተቋም እንዲመሰረት፣ የራድዮና የቴሌቪዥን ስርጭት ሽፋን እንዲጨምር፣ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ከቢቢሲ ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲፈጥርና፣ የሚዲያ ድርጅቶች እንዲቋቋሙ በመታገል ጥሩ ውጤቶች ያስገኘው ይመስለኛል፡፡ የጋዜጠኞች ማህበር እንዳዲስ እንዲደራጅም አስተዋጽኦ አድርጌአለሁ፡፡ ሆኖም ግን ሥራው ሁሉ በኢህአዴግ አመለካከትና ፍላጐት እንዲመራ ነበር አጥብቴ ስንቀሳቀስ የነበረው፡፡ ስለሆነም የጋዜጠኞች የሙያ ነፃነት እንዲጣስ አድርጌአለው ይህም ያሳዝነኛል፡፡

***ህዝባዊ:*** *ሌላው እንግዲህ ህገ መንግስቱ በሚረቅበት ወቅት በሊቀ መንበርነት የመሩት እርስዎ ነበሩ፡፡ ይህን የህገ መንግስቱ መፅደቅ እንዴት ይመለከቱታል? ህገ መንግስቱን አሁን ተመልሰው ሲያዩት ጎድሎታል ብለው የሚያዩት ነገር አለን?*

**ዶ/ር ነጋሶ:** በሕገ መንግስቱ አርቃቂ ኮሚሽን ውስጥ አባል ነበርኩኝ፡፡ የሕገ መንግስቱ አጽዳቂ ጉባኤንም በሊቀመንበርነት መርቻለሁ፡፡ በነዚህ ሂደቶች ተሳትፎ ይህ ዲሞክራሲያዊ የሆነ ሰነድን አገራችን እንድታገኝ በተደረገው እንቅስቃሴ መሳተፌ ኩራት ይሰማኛል፡፡ ያኔም ሆነ አሁን ይህን ህገ መንግስት ተግባራዊ እንድናደርግ ነው ፍላጐቴ ዲሞክራሲአችን ወደ ላቀ ደረጃ እንዲደርስ የሚረዱ ሃሳቦች ካለ ለዚህ ዓላማ ህገ መንግስቱን ማሻሻል ነው እንጂ በሕገ መንግስቱ የተከበሩ መብቶች እንዲሸረሸሩ ወይም ሕገ መንግስቱ እንዲቀለበስ አልፈልግም ይህ ሕገ መንግስት ዲሞክራሲያዊ ነው ብዬ በምንም በማርቀቁና በማጽደቁ ሂደት ላይ ግን ስህተት ፈጽመናል የሚል እምነት አለኝ፡፡ ይህ ስህተት ከላይ ከጠቀስኩአቸው የድርጅቶች ጉዳይ ጋር ይያያዛል፡፡ ባገራችን ነባር የነበሩና በህብረተሰቡ ውስጥ ተሰሚነት ወይም መሰረት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች በተገለሉበት ሁኔታ ነበር ሂደቱ የተጠናቀቀው በመሆኑም ችግሮች እስካሁን ይታያሉ፡፡ ሂደቱ ዲሞክራሲያዊ አልነበረም፡፡ ወንጀል የሌለባቸው የኢሰፓ ሰዎች እንደገና በተደራጁበትና ኢህአፓ መኢሶን ኦነግና ሌሎች ድርጅቶች በነበሩበት የሃሳብ ፍጭት ከተካሄደበት በኋላ ሕገ መንግስቱ ቢፀድቅ ኖሮ ይሻል ነበር፡፡

ከህገ መንግስቱ ይዘት አህኳያ አንዳንድ መሻሻሎች ቢደረጉ ይጠቅማል ብዬ የማምንባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ ከህግ አወጣጥ አኳያ ለፕሬዚዳንቱ የተሰጠው ስልጣን በቂ አይደለም፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የስልጣን ዘመን ቢገደብ ጥሩ ነው፡፡ የሕገ መንግስት ጉዳዮች ፍ/ቤቶችን ማቋቋምም ጠቀሜታ አለው፡፡

**ህዝባዊ፤** *ከህገ መንግስቱ ሳንወጣ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 39 አገሪቱን የሚበታትን ነው የሚል አስተያየት ይሰነዘራል፣ እርስዎ የአንቀፅ 39 እና አገራዊ አንድነት ትስስሩ እንዴት ያዩታል?*

**ዶ/ር ነጋሶ፤** የህገ መንግስቱ አንቀጽ 39 እና የፌደራል ስርዓት አገርን ይበታትናል የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ በኔ እምነት አገርን ሊበታትን የሚችለው በአገራችን የነበሩ ቁስሎች ያለመዳንና ቁስሎቹ የሚብሱበት ሁኔታ ሲፈጠር ነው፡፡ የፌዲራል ስርአት በትክክል ተግባራዊ ያለመሆኑ መሸርሸሩና አንቀጽ 39 በትክክል ያለመከበሩ ነው ያለመግባባትና ግጭትን የሚያስከትለው ያለመግባባትና ግጭት ደግሞ አገር የምትበታተንበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ አንቀጽ 39ኙና የፌዲረል ስርአትን የፈለግነው እኮ የነበሩትን ቁስሎች ለማዳን ነው፡፡ አንቀጽ 39 የጭቁን ህዝቦች ዋስትና ነው፡፡ ለጨቋኞች ማስጠንቀቂያ ነው፡፡

እውነት አንድነትን የሚፈልጉ አገር ወዳድ ግለሰቦች ወይ ቡድኖች የከዚህ በፊቱ ዓይነት ጭቆና እንዳይመጣ ካልተከላከልንና ፍትሃዊ የሃብትና የስልጣን ክፍፍል እንዲኖር ካላደርግን አገሪቱ ትበታተናለች ብለው እንዲያስቡና በአገሪቱ እውነተኛ የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ተመስርቶ እንዲጠናከር እንዲሰሩ ያስታውሳቸዋል:: በሌላም በኩል አንቀጽ 39 መኖሩ፣ ዲሞክራሲ የምንለው ጽንስ ሃሳብ የተናጠል ዜጎችና፣ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብቶች መከበርንም የሚያጠቃልል መሆኑን ያስታውሰናል:: ዜጎች ጠንካራ አገር ወዳድ ሊሆኑ የሚችሉት መሰረታዊ የዲሞክራሲያዊና የሰብአዊ መብቶቻቸው ሲከበሩላቸው ነው:: ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች በሚኖሩበት አገራችን ልክ እነደተናጠል ዜጎች ሁሉ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የሉዓላዊና የዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ሲከበሩ ነው ተከባብረው በጋራ በመኖር የአገርን አንድነት የሚያጠናከሩት:: ከዚህ አኳያ ነው አንቀጽ 39 እና አገራዊ አንድነት ትስስር አላቸው ብዩ የማምነው::

***ህዝባዊ፤*** *ኢህአዴግን ከመልቀቅዎ በፊት የአገራችን ፕራዝደነት ነበሩ:: በዚህ በፕሬዝደንትነትዎ ቦታ ደስተኛ ነበሩን? ህገ መንግስቱ በሚፈቅድልዎ መሰረት የፕሬዝደንትነትዎን ስልጣን ተጠቅመውበታልን? በፕሬዝደንትነትዎ ወቅት ለኢትዮጵያ ህዝብ ይጠቅማል ብለው የሰሩት ዋናው ነገር ምን ይምስልዎታል?*

**ዶ/ር ነጋሶ፤** በግልጽ እንደሚታወቀው ፕሬዚዳንትም ሆኜ የኢህአዴግ/ኦህዴድ አባልና የአመራሩ አካላት አባል ነበርኩኝ:: እስከ 1993 ዓ.ም በነበረው የኢህአዴግ/ኦህዴድ የነበረውን ፕሮግራም አምኜበት በደስታ የድርጅቱ አባል ሆንኩኝ:: የድርጅቱ አባል እስከሆንኩኝ ድረስ  የሚሰጠኝን ተልእኮ በደስታ ተቀብዮ ግዴታዮንና ሃላፊነቴን ለመወጣት ጥረት አደርግ ነበር:: የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲሁም የማስታወቂያ ሚኒስቴር የሆንኩት በዚህ ዓይነት ነበር:: ፕሬዚዳንትም የሆንኩት በዚህ ሁኔታ ነበር:: በስራ ላይ ችግሮች ቢያጋጥሙም በድርጅት በፕሮግራም ውስጥ በተጠቀሱት ዓላማዎችና ግቦች ስምምነት እስካለ ድረስ ግዴታና ሃላፊነትን በደስታ ነው የምትወጣው:: እስከ 1992 ዓ.ም ድረስ በፕሬዚዳንትነት ቦታዮ ደስተኛ ነበርኩኝ:: የቦናፓርቲዝምን ጽሑፍ በ1992 ዓ.ም መጀመሪያ አካባቢ ካየሁ በኋላ የፕሮግራም ለውጥ ገፍቶ እየመጣና ወደየትኛው አቅጣጫ እያመራን እንዳለ ከተገነዘብኩኝ በኋላ ደስተኛ አልነበርኩም:: በመጨረሻም ከድርጅቱ አመራር በሰኔ ወር እንዲሁም ከድርጅቱ አባልነት በነሐሴ ወር ለቀቅሁ:: ስለሆነም ድርጅቱ የሚመራውን መንግስት በመወከል መቀጠልን ስላልፈለግሁ የስልጣን ዘመኔ እስኪያልቅ በቦታው  መቆየቱ በጣም ከባድ ስለ ነበር ደስተኛ አልነበርኩም::
በስልጣን መጠቀምን በተመለከተ በህገ መንግስቱ በአንቀጽ 28/2፣71፣ እና 82/2/ሀ በተዘረዘሩት መሰረት ስልጣኔን ተጠቅሜአለሁ፣ ተግባራትንም ፈጽሜአለሁ:: በዚህ ላይ ችግር አልነበረም:: ይልቁንም ችግር የነበረው የርዕሰ ብሔርን ምንነት በተመለከተ በሕገ መንግስቱ ወይም በሕግ ያለመለየትና ያለመዘርዘሩ ነው:: ባገራችን በርዕሰ ብሔርና በርዕሰ መስተዳደር የሚሉት ፅንስ ሃሳቦች መሀከል ያለው ልዩነት በደንብ ተብራርቶ ሕዝቡ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲፈጥር አልተደረገም:: ምሳሌዎችን ልጥቀስ ሩቅ ሳንሄድ በቅርቡ የኢህአዴግ ልሳን የሆነው አብዮታዊ ዲሞክራሲ ጋዜጣ ሐምሌ 28/1996 ባሰራጨው የ14ኛ ዓመት ቅፅ 2 ቁጥር 123 ገጽ 19 ላይ ስለጠቅላይ ሚኒስተሩ ሲናገር «ርእሰ ብሄር» ይላቸዋል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዳግም የጠቅላይ ሚኒስትሩን ባለቤት «First Lady» የማለት ጋጋታ ተጧጡፎል:: እነዚህ በዥታዎች እንዳይኖሩ በሕገ መንግስቱ ወይም በሌላ ሕግ ዝርዝር መመሪያዎች መውጣት አለባቸው:: ይህ ግን አልተደረገም::
ለምሳሌ ያህል አንድን አገር ወደ ውጭ የሚወክል በዓለም መድረኮች ኢትዮጵያን ወክሎ መገኘት ያለበት ርዕሰ ብሔሩ እንጂ ርዕሰ መስተዳደሩ አይደለም:: አገሪቱን ከሌሎች አገሮች ጋር በማስተዋወቅና የህዝብ ለህዝብ መልካም ግንኙነት እንዲፈጠር እንዲጠናከር ለማድረግ ፕሬዚዳንቱ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል:: በአገር ውስጥም በፌደራል መንግስትና በክልሎች መሀከል፤ በክልሎች መሀከል፣ በብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች መሀከል፣ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መሀከልና በፓለቲካ ድርጅቶች መሀከል መልካም ግንኙነት እንዲጠናከር ከርዕሰ ብሔሩ ብዙ ይጠበቃል:: ርዕሰ ብሔሩ ወደ ውስጥም (በአገር ውስጥ) ወደ ውጭም ያገሪቱ የጋራ የሆኑትን ዕሴቶች (Values) ያስተዋውቃል እንዲጨበጡም ሳያቋርጥ ይቀስቅሳል:: ርዕሰ ብሔሩ ባደጋና በሐዘን ጊዜ እንዲሁም በደስታ ጊዜ በህዝቡ መሀከል እንዲገኝ ይጠበቃል:: ሕገ መንግስቱ ወደ ላቀ ሁኔታ እንዲሻሻል ሃሳብ ያቀርባል::ሕገ መንግስቱ እንዳይጣስ፣ እንዳይሸረሸርና እንዳይቀለበስ ይከላከላል:: የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች ሲጣሱ ዝም ብሎ ማየት የለበትም:: መብቶች እንዲከበሩ፣ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድና ጥፋተኞች ተገቢ ቅጣት እንዲያገኙ ጥሪ ያቀርባል:: እነዚህንና ሌሎች ተመሳሳይ ስራዎችን ለመስራት ዕድል አግኝቼአለሁ ወይ ለሚለው ጥያቄ መልሴ አይደለም ነው:: ከላይ እንደገለፅኩት እነዚህ ጉዳዩች በሕገ መንግስቱም ሆነ በሌላ ህግ አልተዘረዘረም:: በሌላ በኩል ግን ከ 80%-85%ጊዜዬን ለድርጅት ስራ ነው ስጠቀም የነበረው:: የድርጅቱ ፍላጐት ይህ ነበር:: ስለ ሆነም ከህዝቡ ብዙ ትችቶችና ነቀፌታዎች ይሰሙ ነበር:: ይህን ሁኔታ ስለተረዳሁ አንዴ ሁለቴ በጉዳዩ ላይ ጥናት እንዲካሄዱና ሃሳብ እንዲቀርብ አድርጌ ትላልቅ ሰነዶችን ለሚመለከታችው ሁሉ አቅርቤ ነበር:: ለጉዳይ ትኩረት የሰጠው ሰው የለም::
በፕሬዝዳንትነቴ ወቅት ለኢትዮጵያ ህዝብ ይጠቅማል ብለህ የሰራኸው ዋናው ነገር ምንድነው ብለህ ለጠ የቅከኝ ለመመለስ የማነሳቸው ሶስት ጉዳዩች አሉ:: አንደኛው የአልማ ቴሌቶን ነው:: የኦሮሚያ ልማት ለመላው አገሪቱም ትልቅ አስተዋፅኦ አለው የሚል እምነት ነበረኝ፣ አሁንም ይህን እምነት አለኝ:: ስለሆነም በ112 ሚሊዮን ብር ያስገኘውን ቴሌቶን ዝግጅት በመምራቴ እኮራበታለሁ:: ሌላኛው ጉዳይ ስለ

ኤች አይ ቪ ኤድስ ላገራችን ያለው አደገኛነት ግንዛቤ እንዲፈጠር አንድ ብሔራዊ ምክር ቤት እንድቋቋም ሲደረግ በነበረው እንቅስቃሴ ንቁ ተሳትፎ አድርጌአለሁ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ያገራችንን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ በተደረገው ትግል እስተዋጽዔን ለማበርከት በየመድረኩ ተነቀሳቅሻለሁ፡፡ አሁን ከጀርመንና ከቻይና ጋር ያለው መልካም ግንኙነት መሰረቱም የተጣለው እኔ ፕሬዚዳንት በነበርኩኝ ጊዜ ነው፡፡ ከነዚህና ከሌሎች እንቅስቃሴዎች የበለጠ ግን በዋናነት የማነሳው ሶስተኛ ነጥብ በሰኔ 15 ቀን 1993 ዓ.ም የኢህአዴግን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ምክር ቤት ለመልቀቅ መወሰኔና ወሳዬን ይፍ ማድረጌ ነው፡፡ ከዚህ ክስተት የኢትዮጵያ ህዝብ መልካም ትምህርት ቀስሚአል የሚል ተስፋ አለኝ፡፡ ሊመጣ የሚችል ችግርና አደጋ ለመጋፈጥ ዝግጁ በመሆን ያንን እርምጃ መውሰድ ቀላል ነገር አይደለም፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በዚያን ዕለት የፕሬዚዳንት ስልጣኔን ብለቅ ኖሮ መንግስት ችግር ውስጥ መግባቱና በአገሪቱም ያለመረጋጋት ሊፈጠር ይችል ነበር፡፡ ይህ እንዳይሆን ነበር እስከ ስልጣን ዘመኔ መጨረሻ ዕለት ድረስ የቆየሁት፡፡ ይህን ያደረግሁበት ምክንያት ሂደቶች በስርዓት፣ በሕገ መንግስቱ፣ በህጋዊና በሰላማዊ መንገድ እንዲሆኑ የጠበቀ እምነት፣ ስላለኝ ነው፡፡ ከዚህም የኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅም አግኝቶበታል የሚል እምነት አለኝ፡፡

***ህዝባዊ፡*** *በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወቅት ሉአላዊታችን እንዲከበር ጠንክረው ከተሟገቱት ውስጥ አንዱ ነበሩ ይባላል፡፡ በዛን ወቅት የያዙት አቋም አሁን ተመልሰው ሲያዩት እንዴት ይገመግሙታል?*

**ዶ/ር ነጋሶ፡** እርግጥ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወቅት ሉአላዊነታችን እንዲከበር ጠንክረው ከተሚገቱት ውስጥ አንዱ ነበርኩኝ፡፡ በዚህ እኮራበታለሁ፡፡ ድል ካገኘን በኋላም ጦርነቱ ቁሞ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ለማድገና ውሳኔያችንም ትክክል ነበር፡፡ የድል አድራጊነት ዕድላችንን በመጠቀም አሰብ፣ ምፅዋንና አስመራን መያዝ አለብን የሚለውን አዝማሚያ የያዙትን ከሚቃወሙት ጐራ መሆኔ ደስ ይለኛል፡፡ ሆኖም የአልጀርሱ ስምምነትን የሚያፀድቅ አዋጅ ለፊርማ ወደኔ ሲመጣ ባንድ ነጥብ ምክንያት መፈረም አልነበረብኝም፡፡ የፍ/ቤቱን ውሳኔ ያለቅድመ ሁኔታ እንደመጨረሻ ውሳኔ እንቀበላለን ብሎ መወሰን ትክክል አልነበረም፡፡ የሊግ ኦፍ ኔሽንን ኢፍትሃዊ ውሳኔንና የተባበሩ መንግስታትን ኢፍትሃዊ ማዕቀብ መርሳት አልነበረብንም፡፡ በፍ/ቤቱ ውስጥ እንዲያገለግሉ የተመረጡ ግለሰቦች ሰዎች እንደመሆናቸው መጠን ስህተት ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ መጠራጠርና መገመት ነበረብን፡፡ ስለሆነም የአልጀርሱን ስምምነት በዚያ መልኩ ተቀብለን መፈረማችን ይቅርታ ሊደረግለት የማይገባ ስህተት ነው፡፡ በዚህ እኔም ተጠያቂ ነኝ፡፡ በተረፈ የድንበር ኮሚሽኑ ወይም ፍ/ቤቱ የፈፀመውን ስህተት መጠቆሙና በተባበሩት መንግስታትና በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ በኩል ማስተካከያ እንዲፈለግለት ስህተት በስተቀር ያኔም አሁንም ግፊት ማድረጉ አስፈላጊ መሆኑን አምንበታለሁ፡፡ ስለሆነም ባልጀርሱ ውል በመፈረም ሂደት ስፈፅም ነው የነበረኝና ያለኝ አቋም ትክክለኛ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

***ህዝባዊ፡*** *ኢህአዴግና ኦህዴድን ለቀው የወጡበት ዋናው ምክንያት ምን ነበር? በክፍፍሉ ወቅት በተደጋጋሚ ያቀረቡት የነበር ስሞታ ሲታወስ በፕሬዝደንተነትዎና በድርጅት አባልነትዎ ውስጥ ብዙ ጣልቃ ገብነቶች እንደነበሩ ነው፡፡ ይህ እስከምን ድረስ እውነት ነው? በዚህ ዙርያ ከሚሰሙት ውስጥ ቴሌፎንዎን እስከ መቁረጥ የደረሰ እርምጃ እንደነበር ይነገራል፡፡ የጀነራሎች ማስፈራሪያና ጫናም እንደደረሰበዎት ይነገራል፡፡ ይህ እውነትነቱ እስከምን ድረስ ነው?*

**ዶ/ር ነጋሶ፡** ኢህአዴግንና ኦህዴድን ለቅቄ የወጣሁበት ዋናው ምክንያት የድርጅቱ አመራር ኦፓርቹኒስትና አታላይ መሆኑን ስላረጋገጥኩ ነው፡፡ ከሰኔ 10 ቀን እስከ ሰኔ 15 ቀን 1993 ዓ.ም በኢህአዴግ ም/ቤት ስብሰባ ላይ በተሳተፍኩ ጊዜ ነበር ይህን ያረጋገጥኩት እንደሚታወቀው የ1982 የኢህአዴግ ፕሮግራም አቅጣጫ ወደ ሶሻሊዝም የሚያመራውን የአብዮታዊ ዲሞክራሲ አቅጣጫን እንከተላለን የሚል ነበር፣ በስብሰባው ላይ የተገለፀልን ይህን አቅጣጫ እንደምንከተል ከ1983 ወዲህ በይፋ መግለጽ ተውን የኢህአዴግ መሪ ፓርቲንም (ማሌ) ስም እንኳ ማንሳት ተውን የሚል ማብራሪያ ተሰጠ፡፡ ይህን ለምን አደረጋችሁት ሲባል ባንድ በኩል ከምዕራባውያን አገሮች በተለይም ከአሜሪካ የምናገኘውን ድጋፍ እናጣለን ብለን በመፍራት በሌላ በኩል ደግሞ በደርግ/ኢሠፓ ምክንያት ህዝቡ ሶሻሊዝም የሚለውን ቃል መስማትን ጠልቶት ስለነበር አቅጣጫችንን ይፋ ካደረግን የህዝብን ድጋፍ እናጣለን ብለን ፈርተን ነው ተባለ፡፡ ለኔ አንድ ድርጅት የሌሎችን ድጋፍ አጣለሁ ብሎ የሚያምንበትን አቅጣጫ የሚደብቅ ከሆነ አታላይና ኦፓርቹኒስት ነው፡፡
ለኔ ዋናው የታየኝ የኢህአዴግ አመራር ስህተት ከሶሻሊዝም አቅጣጫ ወደ ነጭ ካፒታሊዝም አቅጣጫ መለወጡ ሳይሆን አምንበታለሁ፣ እከተለዋለሁ፣ ተግባራዊ አደርጋለሁ ብሎ በፕሮግራምና በአደረጃጀት ያስቀመጠውን አቅጣጫ የሌሎችን ድጋፍ አጣለሁ ብሎ በመፍራት መደበቅ ነው፡፡ ለነበረው አቅጣጫ ብዙ መስዋእትነት ተከፍሎበታል፡፡ ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ አቅጣጫን ደብቀው ከቆዩ ከብዙ ዓመታት በኋላ የነበረውን ሁኔታ በመግለጽና የምንከተለው አቅጣጫ ነጭ ካፒታሊዝምን ነው ብሎ ለግሎባላይዜሽን (ለኔ ግሎባላይዜሽን አንዳንዱ አወንታዊ ገጽታዎች ቢኖሩትም በመሰረቱ ኢምፔሪያሊዝም ነው) መንበርከክ ሊዋጥልኝ አልቻለም፡፡ እነዚህ ሰዎች በፕሮግራማችን ያስቀመጥናቸውን ሌሎች ጉዳዮችንም ሆነ በሕገ መንግስታችን ያሰፈርናቸውን ነጥቦችንም ለይስሙላ ነው እንደግፋለን የሚሉት የሚሉ ሀሳቦች መጡብኝ፡፡

ከየካቲት 1993 ዓ.ም ጀምሮ ሲወስዱ የነበሩ አንዳንድ መጥፎ እርምጃዎችም ተታወሱኝ:: ስለዚህ ሰኔ 14 ቀን 1993 ዓ.ም ሐሙስ ሌሊት ሳሰላስል አደርኩና ወሰንኩ:: ሰኔ 15 ቀን አርብ ጥዋት ወደ ስብሰባው ሄጄ ውሳኔዬን ይፋ አደረግሁ::

በክፍፍሉ ወቅት አንዳንድ ይከሰታሉ ብዬ ያልጠበቅሁት ሁኔታዎች ተፈጠሩ:: የመጀመሪያው ክስተት የኦህዴድ ሥአኮ ለኢህአዴግ ሥአኮ በፃፈው ደብዳቤ ዙሪያ ነው:: በህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ውስጥ ክፍፍል እንደተከሰተ የኢህአዴግ ሥአኮ አስቸኳይ ስብሰባ ተጠራ:: ስብሰሳውን የጠራው የኢህአዴግ ምክትል ሊቀመንበር ነበር:: ከህወሓት ማ/ኮ የተገለሉት የኢህአዴግ ሥአኮ አባላት በስብሰባው ላይ መሳተፋቸውን ካላረጋገጥን ኦህዴድ በስብሰባው ላይ መገኘት አይችልም የሚል ውሳኔ ላይ ደረስን:: በስብሰባችን ላይ የተስማማነውና እንዲላክ በተረቀቀው ደብዳቤ መሀከል ልዩነት ተከሰተ:: ከኦህዴድ ሊቀመንበር ጋር በስልክ ተጣላን:: ቀጥሎ ብዙ ቀናት ሳያልፉ ሶስት የመከላከያ ሰራዊት ጄኔራሎች (የኦህዴድ መስራቾች) እኔን የኦህዴድን ሊቀመንበርንና ሌሎች ጥቂት የኦህዴድ ማ/ኮ አባላትን በጋራ አግኝተውን የኢህአዴግና ሊቀመንበር ወገን ካልደረፍን በኦህዴድ ውስጥ፣ ኦሮሞ በሆኑ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ውስጥና በኦሮሞ ህዝብ ውስጥ እናንተ የትግሬ አሽከሮች ናችሁ ብለን እናጋልጣችኋለን ብለው አስፈራሩን::

ከዚያ ቀጥሎ የመጣው ክስተት የመቀሌው የካደሬዎች ስብሰባ እየተካሄደ በነበረበት ጊዜ የተፈጠረው ሁኔታ ነው:: በዚያን ወቅት በቢሮዬ የኦህዴድ ማ/ኮ ስብሰባ እየተካሄደ ነበር:: አንድ ቀን ጥዋት ቢተው ከኦህዴግ የመጣ ፋክስ አለ፣ ገብቼ እንዳልሰጥህ በር ላይ እንዳልገባ ከለከሉኝ አለና በሞባይል ስልክ ደወለልኝ:: ከስብሰባ ወጣሁና ጠባቂዎችን ለምንድነው ብዬ ብጠይቅ ከላይ አካል ታዘን ነው ከተገለሉት የህወሓት ማ/ኮ አባላት ማንም ነጋሶ ጋ እንዳይገባ ታዘናል አሉኝ:: ይህ እንደ አንድ ዜጋ፣ እንደ ኦህዴድ አመራር አባልም ሆነ እንደ ርዕስ ብሔር መብቴን መጋፋት ነበር:: ሌላው ክስተት ከመቀሌው ስብሰባ በኋላ በተካሄደው ስብሰባ ላይ የወረዱብኝ የሀሰት ውንጀላዎች ናቸው:: «የአንጃው ደጋፊ ነህ! እነ ተወልደና እነ ገብሩ አንተ ጋ ቤተመንግስት እንደመኖር ሆነዋል! አዘውትራችሁ ለእራት ትገናኛላችሁ» የሚሉ ውንጀላዎች ወረዱብኝ:: በሃሜት ላይ የተመሰረተ ውንጀላ ለኔ በጣም አዲስ ነበር:: ሌላው አዲስ የመጣው ባህል አንዱ ወገን ሌላውን ለመወንጀል የሃሜት ዘመቻ ማካሄድን ነው:: አንድ ሁለት ሰዎች ከኢህአዴግ ሊቀመንበር ጋር በቤቱ እናገናኝህ የሚል ምልጃም ዓይነት አምጥተው ነበር:: ግን አልሄድኩም::

ሌላው ክስተት የጄኔራል መኰንኖች ስንብትና ሹመትን በተመለከተ ነው:: የነ ጄኔራል ፃድቃን መሰናበትና የጄኔራል አባዱላ ከሰራዊት መሰናበትና በመከላከያ ሚኒስቴርነት መሾም ህገ መንግስቱንና በሱም ላይ ተመስርቶ የወጣውን ሕግ ያስቀመጣቸውን አሰራሮች ጥሶአል:: የፕሬዚዳንቱን ስልጣን ተጋፍቶአል፣ ሌላው ጣልቃ ገብነት የኢህአዴግ ሊቀመንበር የኦህዴድን ስብሰባ ለአንድ ወር ያህል መምራት ነው:: በአንፃሩ ግን በክፍፍሉ ጊዜ በኢህአዴግ ም/ቤት ስብሰባ ላይ የህወሓት አመራር የራሱን ህገ ደንብ ለምን ጣሰ ተብሎ ጥያቄ ሲቀርብ የድርጅቱ ሊቀመንበር በህወሓት የውስጥ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባት አትችሉም ብለው በቁጣ መልሰውልናል::
ሌላው ጣልቃ ገብነት በግንቦት 20 ቀን 1993 ዓ.ም ቀትር ላይ የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑ የመከላከያ ሰራዊት አባላት (በተለይ ከፍተኛ መኰንኖች) ከኦህዴድ ማ/ኮ አባላትና ከፍተኛ ካድሬዎች ጋር በጨፌ ኦሮሚያ ጽ/ቤት ያካሄዱት ስብሰባ ነው:: እነዚህ ሁኔታዎች ተጨማምረው ከኤህአዴግና ከኦህዴድ አመራር አባልነት እንድለቅ ያነሳሱኝ:: በኋላም በነሐሴ ወር በነቀምቴ በተካሄደው የ1993 ዓ.ም የኦህዴድ ጉባኤ ላይ እንድሳተፍ ስላልተጋበዝኩ በዚህ የአንድን አባል መብት በማያከብር ድርጅት ውስጥ አባል መሆን ትክክል አይደለም በማለት ይፋ ደብዳቤ ጽፌለት ድርጅቱን የለቀቅሁት::
የቴሌፎን መቁረጥን በተመለከተ ከሰኔ 15 ቀን 1993 ማታ እስከ ሰኔ 17 ቀን ሌሊት የቢሮዬም ሆነ የመኖሪያ አካባቢዬ ስልኮች መስራት አቋርጠው ነበር:: ይህ ሆን ተብሎ ተቆርጦ ነው ወይስ የመስመር ብልሽት መሆኑን ለማረጋገጥ አልቻልኩም:: ሌላው መረሳት የሌለበት በወቅቱም ሆነ ከዚያም በኋላ በየጊዜው ሲካሄድብኝ የነበረው የሚድያ ፕሮፖጋንዳ ነው::

***ህዝባዊ:*** *ኢህአዴግ ለሁለት ሲከፈል ብዙ የፖለቲካ ውዥንብሮች ተፈጥረው ነበር:: እስከ አሁንም እነዚህ ውዥንብሮች በሚገባ የጠሩ አይመስሉም:: በርስዎ አስተያየት የኢህአዴግ መከፋፈል ምክንያቶች ምንድን ናቸው ብለው ያምናሉ? የእርስዎ አቋምስ ከአንዱ ወይ ከሌላው ጋር የሚስማማ ነውን? ወይስ የራስዎ የተለየ አቋም አለዎት?*

***ዶ/ር ነጋሶ:*** በነገራችን ላይ ኢህአዴግ ለሁለት አልተከፈለም:: የሆነው በህወሓት ውስጥ ልዩነቶች ተፈጥረው የድርጅቱ አመራር ለሁለተ ተከፈለ:: አንደኛው ወገን ራሱን ከስብሰባ አገለለ ሌላኛው ወገን ስልጣኑን ለራሱ አጠቃለለ:: «አንጃ» የተባለው ወገን ከድርጅቱ የማ/ኮ ስብሰባ ራሱን ማግለሉን ትክክል ነው ብዬ አላምንም:: በዚያን ወቅት የኔም፣ የኦህዴድ ሊቀመንበርና የደህዴግ የስአኮ አባላት ፍላጎትና ሙከራ «አንጃ» የተባለውን ወገን ወደ መድረኩ እንዲመለስ ነበር፡ በሌላም በኩል የቀረው ወገን ተቻኩሎ

የራሱን የድርጅቱን ህገ ደንብ በመጣስ ጓዶቹን በ «አንጃነት» ፈርጆ ከድርጅቱ ማባረር ትክክል አልነበረም። ይህ ስህተት በወቅቱ በድርጅቱ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ተጠቁሞ እንደነበር አስታውሳለሁ። ከዚያም በኋላ ዲሞክራሲያዊ የሆኑ መድረኮች (በስብሰባም ሆነ በሚድያ) ተፈጥረው ሁለቱም ወገኖች ባሉበት መግለጫ ማብራሪያና ውይይት አልተካሄደም። የህ ያለመሆኑ ያሳዝናል። በአጠቃላይ ችግሮችን በአስተዳደራዊ መንገድ መፍታቱንና «አንጃ» በተባለው ቡድን ላይ ችግሮችንና የመብት ጥሰት በማድረጉ በስልጣን ላይ የቀረው የህወሓት አመራር ስህተት ፈጽሞአል የሚል እምነት አለኝ። ይህ ማለት ግን «አንጃውን» ደግፌአለሁ ወይም እደግፋለሁ ማለት አይደለም። የክፍፍሉ መነሻዎች ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ። በወቅቱ ግን የክፍፍሉ መነሻ የሆነው በቦናፓርቲዝም ላይ የቀረበው ጽሑፍና ለፍሑፉ በተሰጡት የመልስ ጽሑፎች ላይ የተከሰተ ልዩነትና ጭቅጭቅ ነው። እነዚህ ጽሑፎች ሁሉ ጥልቅ ንባብና የርዕዩተዓለም ዕውቀት ይፈልጋሉ። ይህን ጥናት ስላላደረግሁና የርዕዩተ ዓለም ዕውቀትም እስከዚህም ስለሌለኝ፣ ይህ ወገን ትክክል ነው፣ ይህ ወገን ስህተት ነው የሚለው አቋም ላይ አልደረስኩም። ያምሆነ ይህ በዚያን ጊዜ የተፈፀመው ትልቁ ስህተት የነበረውን የኢህአዴግ ፕሮግራም መሰረት በማድረግ የሄድንበትን አቅጣጫ ተግባራዊ በማድረግ ወይም ባለማድረግ የነበረውን ሁኔታ ከመገመገም በፊት፣ አዲስ አቅጣጫን ለማስያዝ የነደፈን የተፀነሰን የቦናፓርቲዝም ጽሑፍ ላይ ውይይት መጀመር ነበር። በተጨማሪም የውይይቱ አካሄድ ዲሞክራሲያዊ አልነበረም። መሆን የነበረበት መጀመሪያ በአጠቃላይ የኢህአዴግ አመራር አባላት ተሳትፎ መሆን ነበረበት። TPLF ብቻውን በአቅጣጫ ላይ መወያየት አልነበረበትም ሁሉም በእኩልነት እንዲሳተፉ መደረግ ነበረበት። አካሄዱ ፓቴርናሊስትክ (አባታዊ) ነበር። ብአዴንም ለሁሉም ድርጅቶች እኩል ተሳትፎ ከመከራከር ይልቅ ለብአዴን ተሳትፎ ብቻ ተከራክሮ ህወሓቶች እምቢ ሲሉ ወደ ራሱ መድረክ መሄዱ ስህተት ነበር። ኦህዴድና ዶህዴግም አገለላችሁን ብለው ያለመከራከራችን ስህተት ነበር።
ሌላ መጠቀስ ያለበት ጉዳይ የብአዴን ሚና ነው። በኔ እምነት የብአዴን ከፍተኛ አመራር አወንታዊ ሚና የተጫወተ አይመስለኝም። ተቻኩሎ ካንዱ ወገን ጋር መወገንና በአብዮቱ አቅጣጫ ላይም በችኮላ መወሰን አሉታዊ ተጽእኖ አድርጐአል። የመከላከያ ሰራዊቱ ከፍተኛ አመራር አባላት በቦናፓርቲዝም ጽሑፍ ውይይት ሂደት እንዲሳተፉ መደረጉም ስህተት ነበር። ይህ መሆኑ የሕገ መንግስታችንን አንቀጾችን መፃረር ነው። አንቀጽ 87/4 «የመከላከያ ሰራዊት በማናቸውም ጊዜ ለሕገ መንግስቱ ተገዢ ይሆናሉ» ይልና በአንቀጽ 87/5 ላይ ደግሞ «የመከላከያ ሰራዊት ተግባሩን ከፖለቲካ ድርጅቶች ወገናዊነት ነፃ በሆነ አኳኋን ያከናውናል።» ይላል።
ሌላ መጠቀስ ያለበት ጉዳይ የአቶ ገብሩ ከስልጣን መነሳትና በተወካዮች ም/ቤት የትግራይ ህዝብ ተወካዮች የነበሩትን ከምክር ቤቱ ኢ ህገመንግስታዊና ህገወጥ በሆነ አኳኋን መካሄዱ ነው። ለማጠቃለል ያህል በቦናፓርቲዝም ዙሪያ በተከሰተው ልዩነት ይህን ወይም የዚያን አቋም የመደገፍ ሁኔታ ላይ ባልደርስም «አንጃ» ተብሎ በተፈረጀው ቡድን ላይ የደረሰውን ኢ ዲሞክራሲዊ አሰራር ግን እቃወማለሁ።

***ህዝባዊ:*** *ከክፍፍሉ በኋላ በአገራችን በርካታ ክስተቶች ታይተዋል። ህገ መንግስቱን የሚፃረሩ በርካታ ሕጎች ወጥተዋል ይባላል። በዚህ ጉዳይ ይስማማሉን? የርስዎ በፖለቲካ መድረክ እንዳይካፈሉ መከልከልስ ሕገ መንግስታዊ ነው ብለው ያምናሉን? ካልሆነ ምን ያሰቡት መፍትሄ አለ?*

***ዶ/ር ነጋሶ:*** ከ1993 «ተሃድሶ» ወዲህ ህገ መንግስቱን የሚፃረሩ ህጐች ወጥተዋል ስለመባሉ ገና እያጠናኋቸው ያሉት ህጐች የከተማዎች ቻርተሮችን፣ የፌደራል ጉዳዮችን ሚኒስቴርን የፌዴራሉ መንግስት በክልሎች ጣልቃ መግባትን፣ የተጠባባቂ ጦርን መመስረትን፣ የፌደራል ፖሊስ፣ የክልል ፖሊስና ሚሊሽያን ግንኙነት፣ አዲሱን የኢንቨስትመንት ሕግና አሰራር በተመለከተ ነው። እነዚህ ህጐችና መመሪያዎች እንዴት ሕገ መንግስቱንና የክልሎችን መብትና ስልጣን እንደሚፃረሩ ገና አልለየሁም። እኔም ብቻ ሳልሆን ሁሉም ዜጋ ሊያጠናቸውና አስተያየት ሊሰጥባቸው ይገባል። ገና በረቂቅ ደረጃ ካሉት ህጐች መሀከል በግልጽ ህገ መንግስቱን የሚፃረረው የፕሬስ ሕግ ረቂቅ ነው። ይህ ሕግ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 29 የተከበረልንን ዲሞክራሲያዊ መብቶች ይፃረራል። ይህን በተመለከተ ጋዜጠኞችና የጋዜጦች አሳታሚ ድርጅቶች ወይም ባለቤቶች ብቻ ሳይሆን ሁሉም ዜጋ ይህ ህግ እንዳይፀድቅ ለማድረግ መታገል አለበት የሚል አመለካከት አለኝ። ይልቁንም አሁን እየተሰራበት ያለውን ህግ የበለጠ ዲሞክራሲያዊ የሚያደርግ ህግ እንደወጣ ወይም በዚህ አቅጣጫ ያለው ህግ የሚሻሻልበትን መንገድ እንዲቀይስ ግፊት ማድረግ አለብን። ከክፍፍሉ በኋላ ህገ መንግስቱን የሚፃረር ህግ ወጥቶአል ተብሎ ከሚጠቀሱ ህጐች አንዱ የፀረ ሙስና ሕግ ነው። በኔ እምነት ትንሽም ሆነ ትልቅ የሙስና ወንጀል በሚፈጽሙ ግለሰቦች ላይ ከባድ የቅጣት እርምጃ መወሰድ አለበት። ለተጠርጣሪዎችም የዋስ መብት መከበር የለበትም የሚል እምነት አለኝ። በዚህ ጉዳይ ላይ ህሊናዬም አይወቅሰኝም።
ሆኖም ግን ሕጉ በሕገ መንግስታችን የተከበሩትን የሰብአዊ መብቶችን የሚፃረር ከሆነ ይህን በተመለከተ፣ መሻሻል አለባቸው የሚባሉ አንቀጾች ተጠቅሰው ከነመሻሻያ አንቀጾች ጋር የማይቀርቡበት ምክንያት አይታየኝም። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በእስር ቤት ያሉ የኢህአዴግ አመራር አባላትን ጨምሮ ጉዳያቸው ውሳኔ ሳያገኝ መጓተቱ ትክክል አይመስለኝም። የተጓተተ ፍትህ የተከለከለ ፍትህ ነው የሚለውን አባባል ማስታወሱ ጥሩ ነው።

ሌላው አዋጅ 255/94 ነው። አዋጁ የኔንም፣ በስልጣን ላይ ያሉትን ፕሬዚዳንትም፣ የወደፊቱን

ፕሬዚዳንትንም <u>የዜግነትና</u> የህገ መንግስታዊ መብቶቻችንን በግልጽ ይፃረራል፡፡ <u>እኔን</u> በተመለከተ በአንቀጽ 7 ላይ «ፕሬዚዳንቱ በስራ ዘመኑም ሆነ የስራ ዘመኑ ካበቃ በኋላ ወገንተኝነት ካላቸው የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች የመገለል ሃላፊነት ይኖረዎል» የሚለው የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 8/3 (የተሳትፎ ጉዳይ) ፤ አንቀጽ 9/2 (ሕገ መንግስቱን የማስከበርና ለሱም ተገዥ መሆን) ፤አንቀጽ 29/1-2 (የአመለካከትና ሃሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብትን) አንቀጽ 30/1 (የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብትን) አንቀጽ 31 (የመደራጀት መብትን) ድንጋጌዎችን  በግልጽ ወይ እንዲሻሻል አልያም ከነጭራሹ እንዲቀር ለሁለቱ ም/ቤቶች አቤቱታዮን ካቀረብኩ ይኸው አንድ ዓመት ተኩል ሆኖአል፡፡ እስካሁን መልስ አላገኘሁም ትግሌን እቀጥላለሁ፡፡